## ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)

## 24 ኛ ሳምንት

### በገና ደርዳሪው ዳዊት ጎልያድን አሸነፈ

**የትምህርቱ ዓላማ**

- ስለ ንጉሥ ዳዊት የጀመርነውን ትምህርት መቀጠል።

**ምንባብ**

- 1ኛ ሳሙ. 16 እና 17

**መግቢያ**

- የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን የተመረጠው ሳኦል ነበር።
- ሳኦል ግን በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር አልታዘዝምና የእግዚአብሔር መንፈስ ተለይቶት በርኩስ መንፈስ ይሠቃይ ነበር።
- በዛሬው ትምህርታችንም ዳዊት በሳኦል የነበረውን ሰይጣን እንዴት እንዳራቀለትና ንጉሡና እስራኤልን ረድቶ ጎልያድን ያሸነፈበትን ታሪክ እንማራለን።

**ትምህርቱ**

- ሳኦል ለእግዚአብሔር ሳላልታዘዝ የእግዚአብሔር መንፈስ ራቀው። ርኩስ መንፈስም ያሠቃየው ነበር። በገና ደርዳሪ እንዲጠሩለት አገልጋዮቹን አዛዙ።አገልጋዮቹም የእሴይ ልጅ ዳዊት ጥሩ በገና ደርዳሪ እንደሆነ ለሳኦል ነገሩት።
- ሳኦል እሴይ ልጁን ዳዊትን እንዲልክለት ላከበት። እሴይም ዳዊትን አህያ ሰጥቶ፣ ምግብና ወይና አስይዞ ወደ ሳኦል ላከው። ሳኦል ዳዊትን ሲያየው በጣም ወደደው ሾመውም። ስለዚህ ሳኦል ከዳዊት ጋር መኖር ጀመረ በገና ይደረድርለትም ነበር።
- ዳዊት በገና ሲደረድርም ሳኦልን የሚያሰቃየው ርኩስ መንፈስ ይርቅለት ነበር።
- ዳዊት በገና የመደርደር፣ በመዝሙር እግዚአብሔርን የማመስገንም ጸጋ ነበረው። ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው 'መዝሙረ ዳዊት' ዳዊት ለእግዚአብሔር ያቀረባቸው ምሥጋናዎች ናቸው።
- ዳዊትም አባቱንና ሳኦልን እያገለገለ ኖረ።
- አንድ ቀን ፍልስጤም ከእስራኤል ጋር ሲዋጉ ወጡ። ጎልያድ የተባለ ግዙፍ ሰውም ወጥቶ ከእኔ ጋር መዋጋት የሚችል አንድሰው ይምጣ አለ እስራኤልንም አዋረደ በእግዚአብሔር ያላቸውንም እምነት ናቀባቸው።
- እስራኤልም ጎልያድ ግዙፍና ጠንካር ስለነበረ ፈሩ። ዳዊት ግን ወጣት ብላቴና ቢሆንም ጎልያድን አልፈራም፤፤
- ዳዊት ወደ ሳኦል ቀርቦ በጎቹን ከአንበሳና ድብ አፍ እንዴት ያድን እንደነበር ነገሮ÷ ግዙፉን ጎልያድንም እንደሚያሸንፈው በእግዚአብሔር ታምኖ ተናገረ። ሳኦልም ከጎልያድ ጋር እንዲዋጋ ፈቀደለት።
- ጎልያድ ትንሹን ብላቴና ዳዊትን ሲያየው በንቀት ***"ወደ እኔና÷ ሥጋህንም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ።"*** አለው።
- ዳዊትም ***"አንተ ሰይፍና ጦር ይዘህ ትመጣብኛለህ እኔ ግን .......በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ።"*** አለ።
- ዳዊት ከአረኛ ኮሮጆው አንድ ድንጋይ አውጥቶ ወነጨፈው፣በጎልያድ ግምባርም ተቀረቀረ ግዙፉ ጎልያድም ወደቀ። ዳዊት እግዚአብሔር ድል እንደሚሠጠው አምኖ ግዙፉን ሰው በወንጭፍና ድንጋይ ድል አደረገ።
- እስራኤልም በደስታ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ***"ሳኦል ሺህ ዳዊት አሥራ ሺህ አሸናፈም።"*** አሉ።

**ጥያቄዎች**

1. ሳኦል በእስራአል እንዲነግሥ የሾመው ማነው?
2. የእግዚአብሔር መንፈስ ለምን ከሳኦል ተለየ?
3. ዳዊት ከሳኦል ርኩስ መንፈስ ያርቅለት የነበረው እንዴት ነው?
4. የዳዊት አባት ማነው?
5. እስራኤልን የተገዳደረው/የተሳደበው/ ግዙፍ ሰው ማን ይባላል?እስራኤልስ ለምን ፈሩት?
6. ዳዊትስ ፈርቶት ነበር? ምንስ አለው?

**መዝሙር**

ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ
ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ    መዝ 9÷11

# David & Goliath



ይቆየን፡፡